# ቀድሼ እከፍላለሁ ወይስ ቦድሼ እከፍላለሁ ?

ከምእመናን አንዱ

የፈረንጆች ዓመት አልፎ በሌላ አዲስ ዓመት ተተክቷል። የሃገራችን ሰው ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም ይሉ ነበር ። የፈረንጅ ሃገር ሰው ጉድ ሳይሰማ ጃንዋሪ አይገባም ቢል ደግሞ እንደኛው መስከረም ማለት ነው ። የፈረንጁ አዲሱ ዓመት እንደኛ በሳቅ ያስጀምራችሁ ብዬ ልመርቃችሁ ? በዚህ አዲስ ዓመት በእኛ ላይ የደረሰው ግን ምርቃት ሊሆን አይችልም ። የእኛ ሳቅ የእውነት ምሬት ነውና ከዚህ ያውጣችሁ ብል ይሻላል።

ይህ የማቀርብላችሁ በጀርመን ውስጥ የሚገኙ የሦስት አብያተ ቤተክርስቲያናት ታሪክ ነው ። ብዙም መፃፍ አልችልም። ከጅምሩ ስለማላውቀው የሚያውቁት በሚገባ እንደሚጽፉት አልጠራጠርም ። ለማንኛውም ይህንን ከዚህ በታች የምጽፈውን የቅሌት መዝገብ ከፍቶ ለተመለከተው ምን ያህል እንደዘቀጥን የሚረዳው ይሆናል ።። ነገሩ እንዲህ ነው ።

**<u>ሦስቱ ቤተክርስትያኖች የሚገኙት</u>**

1.በኮለን ከተማ የሚገኘው የቅዱስ ሚካኤል በቄስ መራዊ የሚተዳደር ፣
2. በፍራንክፈርት የምትገኘው የቅድስት ማርያም በአባ ሲራክ የሚተዳደርና
3, በሙኒክ ከተማ የሚገኘው የቅዱስ ገብርኤል በቄስ መስፍን የሚተዳደር ነው ።

እነዚህ ሦስተ ቤተ ክርስቲያኖች በወያኔው አባ ጳውሎስ ሥር የሚተዳደሩ ሲሆኑ ቄስ መራዊ የእነዚህ የበላይ ሆነው ያገለግላሉ።
የአባ ጳውሎስ አስተዳደር ከሥር መሠረቱ የተበላሸ፣ በዚህም አስተዳደር ዙሪያ የተሰበሰቡትም የተበላሹ፣ እንደሆነ ሲነገርው አልሰማም ያሉ ብዙ ምእመናን በእነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች አካባቢ መሰባሰብ ከጀመሩ ሰንብቷል ። እነዚህ ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ካህናት በሙሉ በአፍቅሮተ ነዋይ የተሞሉ ሲሆኑ በጀርመን ውስጥ ከምእመናን የሚገኘውን ገቢ እንደፈለጉ የሚያዙበት የሚያደርጋቸው ማህበር(Eintragen Verein) ለማቋቋም የሚፈቅደውን ሕግ በመጠቀም ነው ።

ነገሩ የተጀመረው ፍራንክፈርት ቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን ነው ። የሰበካ ጉባዔ ምርጫ ሲደረግ የፍራክፈርቱ ማርያም አስተዳዳሪ አባ ሲራክ አቶ አምሃ የሚባል ግለሰብ ካልተመረጠ ብለው አጥብቀው ይከራከራሉ ። ምእመናኖቹ አይሆንም ቢሉም አቶ አምሃ በቄሱ ጥረት ይመረጣል ። ታዲያ አባ ሲራክ ተደስተው ስብሰባው ያልቃል ። አቶ አምሃ ለካ ከቄሱ በላይ ማርያምን ይወድ ነበርና ማርያምን አላታልልም ብሎ ስራውን ይጀምራል ።የገንዘብ ቁጥጥር ይደርጋል ። በዛ ያለ ገንዘብ እንደ ጠፋ ያውቃል ። ቄሱን ስለ ገንዘቡ ቢያነጋግራቸው ከወያኔ ጋር ባላቸው ፍቅር በትምክህት በመሞላት ዞር በል ይሉታል ። ይህ የማርያም ልጅ ነኝ ብሎ የተነሳ ግለሰብ ለጀርመን መንግሥት ባለስልጣናት ሁኔታውን ያጋልጣል ። አባ ሲራክም በትግሬነቴ ይህ ደረሰብኝ በማለት ቤተ ክርስቲያኑን በዘር ለመከፋፈል ጥረት ያደርጋሉ።በቤተክርስትያኑ አካባቢ ያሉትን የትግራይ ተወላጆች ማሰባሰቡን ቢቀጥሉም መጀመሪያ አልተሳካላቸውም ነበር። ወረቀቶች መበተን ሲጀምሩ ጉዱ ሁሉ አደባባይ ላይ ይዘረገፋል ። ቄሱ መውጫ መንገድ ሲያጡ የዘር ችግር ለማድረግ ጥረታቸወን ይቀጥላሉ ።

የጀርመን በአባ ጳውሎስ ሥር ያሉ ቤተክርስቲያኖች ሃላፊ የከለኑ ቄስ መራዊ ይህ ሁኔታ ሰላላማራቸው ምንአልባትም ተዛምቶ እሳቸው በሚመራው ቤተክርስቲያን ውስጥም እንዲህ ዓይነት ችግር ከተፈጠረ የሚያደርሰውን አደጋ በማስተዋል ለማስታረቅ በአደባባይ ሲጥሩ በውስጥም በኩል ደግሞ ይህንን ጉዳይ ያጋለጠውን አቶ አምሃን ለመጉዳት ሴራ ይጀምራሉ ።

ይህ ቁጥጥሩን አድርጎ የገንዘብ ጉድለቱን ያገኘው ግለሰብ ቤተክርስቲያኑ አካባቢ እንዳይደርስ (በጀርመንኛ Houseverbot) በጠበቃ ይታዘዛል ። የደረሰው ደብዳቤ እንደሚጠቅሰው አቶ አመሃ ቤተክርስቲያኑ አካባቢ ቢደርስ ለሚደርሰው ችግር ተጠያቂ እንደሚሆን ነው ። ወያኔዎቹ ይህንን ደብዳቤ ከደረሰው በኋላ ቤተክርስቲያኑ አካባቢ ቢደርስ ብጥብጥ ለማስነሳት ዝግጅት ላይ እንደነበሩ በፍራንክፈርት ከተማ የተወራ ሲሆን አቶ አምሃም በግል የሚደርስበትን ችግር በመረዳትና የጀርመን ሕግ ነውና ወደዛ መሄዱን ያቆማል ። አባ ሲራክም አንዳንድ የትግራይ ልጆችን በማሳመን ነገሩ እንዲቀዘቅዝ ይደርጋሉ ። ውስተ ውስጡን ግን የጀርመን ሕግን ጥሰዋልና በአባ ሲራክ ላይ ምርመራው መቀጠሉ አይቀርም ። በነገራችን ላይ አባ ሲራክ የመኖሪያ ፈቃዳቸውን ያገኙት የፖለቲካ ስደተኛ ሆነው ሲሆን የጀርመን መንግሥት የሚከለክለውን ሕግ ጥሰው በየወቅቱ ወደ ኢትዮጵያ በዚ|ያውም የአባ ጳውሎስን እጅ ለመንሳት አሁንም ይመላለሳሉ ።

በፍራንክፈርት የተጀመረው ጉድ ሌሎችንም ማነቃቃት ይጀምራል ። በሙኒክ ገብርኤል ቤተክርሰረቲያን መሪ በቄስ መስፍን ላይ  ቁጥጥር ይጀመርና መቶ ስድሳ አምስት ሺህ ኤሮ(165000€) ለቤተክርስቲያን ማሠሪያ የተዋጣ ገንዘብ መጎደሉ ይደረስበታል ። ስብሰባ ተደርጎ ቄሱ የት እንዳደረሱት ሲጠየቁ ሂሳብ ስለማልችል ጎደለብኝ ብለው ያሳብባሉ ። ሕዝብ በተሰበሰበበት በትምክህት፣ምን ይመጣብኛል በማለት የጎደለውን ገንዘብ አምነው ይቅርታ ይደረግልኝና **ቀድሼ እከፍላለሁ** ብለው ሃሳብ ያቀርባሉ ።

የእሳቸው መስረቅ አልገረመም። ገና ቁጥጥሩ ሳይጀምር በሙኒክ ከተማ ቄስ መስፍን አዲስ አበባ ውስጥ ቤት ከነ ዋና ቦታው እያሰሩ መሆኑን ያልሰማ አልነበረም ። ጥርጥሩም ቁጥጥሩም የተጀመረው ከዚያ በኋላ ነው ። በጣም የሚገርመው  ቄስ መራዊ የከለሉ ሚካኤልና የጀርመን በወያኔ ሥር የሚተዳደሩ ቤተክርስትያናት አላፊ የሕዝብ ገንዘብ ከማስመለስ ወይም ከማጋለጥ ይልቅ ከቄሱ ጎን በመቆም  አጥብቀው ምህረት ሲጠይቁ መታያታቸው  ነው ። **"ምእመናን መሃሪ ናቸውና ምሕረት አድርጉ"** ብለው ሰበኩ ። ሁኔታው  ነገ በእሳቸው ላይ የሚመጣውን በማሰብ ዛሬውኑ ብልሃት እንደዘየዱ በሆናቸውን ምእመናኑ ገብቷቸዋል ። ለነገሩ ነው እንጂ የከለኑ ቢመረመር ስንት እንደሚሆን መገመት ያዳግታል ? ቄስ መራዊ በዚህ በዘረፋ ልምድ እንዳላቸው ማንም የሚያውቀው ሐቅ ነው ።

ይህ የሙኒኩ የዘረፋ ተግባር  እንደተሰማ ከሁሉ የሚገርመውና የሚያስቀው የፍራንክፈርቱ አባ ሲራክ እኔ ያጎደልኩት አስር ሺህ ብር ያነሰ ሲሆን  ቄስ መስፍን አማራ ስለሆነ ይህንን ሁሉ ሲጎድልበት ምንም አልተባለም ። በእኔ ላይ የጠነከረው ትግሬ ስለሆንኩ ነው ብለው  ሰዎች ሰብስበው ሲያማርሩ ነበር ተብሎ ፍራንክፈርት ውስጥ ተወራ ። ጉድ ሳይሰማ ማለት ይሄኔ ነው ።

በአሁኑ ወቅት የሕዝብ ገንዘብ ተበልቶ መቅረት የለበትም የሚሉ ብዙ መእምናን እንዳሉ የሚታወቅ ነው ። ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤትም መቅረብ  እንዳለበት  ሕዝቡ ያምናልም፣ ይፈልጋልም ። የወያኔ ደጋፊዎችና ቄስ መራዊ በዝምታ ምንም እርምጃ ሳይወሰድ እንዲያልፍ ይፈልጋሉ ። ዛሬ ለእውነት እንዲሠሩ የተመረጡት ኮሚቴዎች ይህንን የሕዝብ ገንዘብ የማስመለስ ሃላፊነት አለባቸው ። በይሉንታና በፍርሃት ካለፉት ግን ከዘራፊው ቄስ መስፍን ወይም ከተባባሪው ከቄስ መራዊ የማይሻሉ ሆነው ነው የሚቀሩት ። ታሪክ ጭራ ነውና ለእውነት መቆም ዛሬውኑ አስፈላጊ ነው ።

**ዛሬ በጀርመን የአባ ጳውሎስ ተወካዮች ዘረፋውን በሰፊው ተያይዘውታል ። ካለአንዳች ተጠያቂነት ምእመናን በተለይም በሙኒክ  የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን  በአካባቢው ከሚደርስባቸው ዘረኝነት ጋር ተዋግተው ፣ ሸንት ቤት ጠርገው ፣ የጉልበት ሥራ ሠርተው ወገባቸው ተበጥሶ፣ በሽተኛ እየሆኑ( ይህንን እያንዳንዱ የጀርመን ነዋሪ የሚውቀው ነው ) መጽናኛ ይሆነናል ብለው፣ ሊያሰሩት ላሰቡት ቤተክርስቲያን  ይውላል ብለው  የሰበሰቡት ገንዘብ እንዲህ በቀን ጅብ ሲበላ ምንኛ እኛነታችን ያስጠላናል ? በአንድ የእግዚሐብሄር አገልጋይ ነኝ በሚል ካህን ይህንን ያህል ግፍ በሃገሩ ሰዎች ላይ ሲያደርስስ ምን ይሰማው ? የዚህስ ካሃን የወደፊት ሕይወት ምን ትመስል? ይህንን ኃጢያት በግፍ በተወሰደ ገንዘብ የተሠራ የዋና ቦታ ያፀዳው ይሆን ? በዘር የሚከፋፍልስ ከሃን እንዴት ሆኖ የቤተክርስትያን አገልጋይ ይሆን ?**

**ውድ ምእመናን**

**እነዚህ የተደራጁ ዘራፊዎች ብቻ አይደሉም ጥፋተኞች ። ምእመናንም ቢሆኑ ይህንን ልቅ የሆነ ዝርፊያ ስንፈቅድ ጥፋቱ ከኛም ነው ።ከበርካታ መእመናን የሚዋጣ ገንዘብ በአንድ ካህን እጅ ያለ ጥንቃቄ እንዲወጣ ለምን እንፈቅዳለን ? ችግሩ ከመድረሱ በፊት ለምን መ፣ፍትሄ አንፈልግም ?  እነዚህ ካህናት በልዩ ልዩ ዘዴ እየከፋፈሉን እንገኛለን። ከአሁን በኋላ በሌብነት እጁ ከቆሸሸ ቄስ መስቀልን መሳለም እንዴት ይቻለን ይሆን ? ቀድሶ ነው ወይስ እንደለመደው ከሕዝብ ገንዘብ ቦድሶ ነው የሚከፍለው ?**

**ከቡራን የጀርመን ድምጽ ራዲዩ አዘጋጆች ፡**

**ሕዝብ እውነትን የማወቅ መብት አለው ። ጋዜጠኞች ደግሞ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው ። እንዚህን ካህናት ፣ የኮሚቴ አባላት ቃለ መጠይቅ በመጠየቅ እውነትን ሕዝብ እንዲረዳው ያስፈልጋል ። በጀርመን ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለጀርመን መንግሥት የሚከፍሉት ቀረጥ ለዚህ ቀን እንኳ ሊረዳቸው ይገባል ። አለበለዚያ ግን የጋዜጠኝነት ግዴታችሁን እንዳልተወጣችሁ ፣ በዚህ ኃጢያት ውስጥ በተዘዋዋሪም እንደገባችሁበት ልትገነዘቡት ይገባል ።**

ከሁሉ የሚገርመኝ እኛ ኢትዮጲያውያን ምን ነካን ? ቅስና ሳይኖራቸው ቆብ በጫኑ ወንበዴዎች ስንዘረፍ ለመቃወም ምነው ፈራን ? አደባባይ ላይ አባ ሲራክ አማራን ሲዘልፉ ምነው ፍርሃት ዋጠን ? ቄስ መራዊ በድብቅ ከወያኔ ጋር ሲደራደር እያወቅን በገንዘብ ስንረዳ አልነበረም ? ቤተክርስቲያን ማሠሪያ ገንዘብ ሲዘረፍ አያገባንም ማለት ምንድነው ? በእንደዚህ አይነት ዘራፊዎች የተመሠረተ ቤተክርሲቲያን ነው ብለን መቀበል ምንድነው ?

እግዚአብሔር ከእንደዚህ ዓይነት ካህናት ይሠውር ።